# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ

## የሠራተኞች የደመወዝ እርከን ጭማሪ እና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 146/2015

ሰኔ 2015 ዓ.ም

**መመሪያ ቁጥር 146/2015**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ**

**የሠራተኞች የደመወዝ እርከን ጭማሪ እና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ አፈጻጸም መመሪያ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የተሰጠውን ግብር እና ታክስ የመሰብሰብ ኃላፊነት በተሟላ መልኩ በመወጣት ለከተማዋ ዕድገትና ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚያስችል በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን ለተከታታይ ሁለት ዓመታትም በገቢ አሰባሰቡ የቢሮው ሠራተኞችና አመራሮች ባደረጉት ርብርብ አዳጊ የሆነ ውጤት እያስመዘገበ የሚገኝ በመሆኑ፤

የተቋሙን የገቢ አሰባሰብ ዕቅድ ስኬታማ ለማድረግ የተደረገውን ጥረት እና የተመዘገበው ውጤት ከፍተኛ መሆኑን መረዳት በመቻሉ እና ለዚህ ውጤት መሳካት አስተዋጽኦ ለነበራቸው የቢሮው አመራሮች እና ሰራተኞች በተቋሙ የተዘረጋን የማትጊያ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ቢሮ የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 99/2010 አንቀጽ 47 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስዳደር ገቢዎች ቢሮ የደመወዝ እርከን ጭማሪ እና የልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 146/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. "ቢሮ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ነው፤
2. "የበላይ ኃላፊ" ማለት ቢሮውን በበላይነት የሚመራ ወይም ምክትሎቹ ናቸው፤
3. "ቢሮ ኃላፊ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የቢሮ ኃላፊ ነው፤
4. "ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች" ማለት የቢሮው ምክትል ኃላፊዎች እና በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የሚገኙ ናቸው፤
5. "ሠራተኛ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ደንብ ቁጥር 99/2010 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 የተሰጠውን ትርጉሜ የሚይዝ ይሆናል፤

6. “ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት” ማለት የቢሮው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፣ የታክስ ማዕከላት እና የማይክሮ ግብር ከፋዮች ጽህፈት ቤት ነው፤
7. “እርከን” ማለት አንድ ሠራተኛ በያዘው የሥራ ደረጃ መነሻ ደመወዝ ትይዩ የሚገኝ የጎንዮሽ ደመወዝ ጭማሪ ነው፤
8. “የስራ መደብ” ማለት በአንድ መንግስት ሠራተኛ ሙሉ የስራ ጊዜ እንዲከናወኑ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤
9. “ደረጃ” ማለት አንድ ሠራተኛ ለተመደበበት የስራ መደብ የተቀመጠ መነሻ ደመወዝ ነው፤
10. “የእርከን ጭማሪ” ማለት አንድ ሠራተኛ በያዘው የስራ ደረጃ መነሻ ደመወዝ ትይዩ የሚገኝ የደመወዝ ዕርከን የጎንዮሽ ጭማሪ ነው፤
11. “የመኖሪያ ቤት አበል ማሻሻያ” ማለት ቀደም ሲል በተቋሙ ተፈቅዶ ስራ ላይ የዋለውን የመኖሪያ ቤት አበል ከወቅቱ የገበያ ዋጋ አንጻር ተመጣጣኝ ማሻሻያ ነው፤
12. “ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች አበል” ማለት የመኖሪያ ቤት አበል፣ የመዘዋወሪያ አበል፣ የሙያ አበል፣ የኃላፊነት አበል እና የሞባይል ካርድን የሚያጠቃልል የአበል አይነቶች ናቸው፤
13. “በተጠባባቂነት መመደብ” ማለት በቅጥር በቂ የሰው ኃይል ሊገኝ የማይችልባቸው ክፍት የስራ መደብ ላይ በደረጃ ዕድገት የሰው ኃይል ማሟላት ባለመቻሉ ከፍ ወዳለ ክፍት የስራ መደብ ላይ ሰራተኛ ወይም ኃላፊን መድቦ ማሰራት ነው፤
14. “በውክልና መመደብ ማለት” አንድ የስራ መሪ በህመም፣ በዓመት የእረፍት ፈቃድ፣ በስራ ጉዳይ ፣በስልጠና ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት በስራ ገበታው ላይ በማይገኝበት ጊዜ በደረጃ ዝቅ ያለ የስራ መሪ ወይም ሠራተኛ የወካዩን ስራዎች በመደበኛ ስራው ላይ ደርቦ እንዲሰራ ማድረግ ነው፡፡

## 3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ያካትታል፡፡

## 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚደረገው በአዲስ አበባ ከተማ አስዳደር ገቢዎች ቢሮ በየደረጃው በመዋቅር በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ በተደለደሉ ሠራተኞች ላይ ብቻ ነው፡፡

## 5. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ የቢሮውን የሰራተኛ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 99/2010 መሠረት በማድረግ የከተማ አስተዳደሩ ለሰራተኞች የሦስት እርከን የደመወዝ ጭማሪ እና የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ እንዲደረግ ያስተላለፈውን ውሳኔ በአግባቡ ለመፈጸም ለማስቻል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የእርከን ጭማሪ እና የጥቅማጥቅም አከፋፈል

### 6. የእርከን ጭማሪው የሚመለከታቸው ሠራተኞች

1. የከተማ አስተዳደሩ ለሠራተኛው እንዲሰጥ በተፈቀደው የደመወዝ እርከን ጭማሪ ውሳኔ መሠረት ሠራተኛው ተመድቦበት በመስራት ላይ በሚገኘው ለደረጃው በተሠጠው የመነሻ ደመወዝ ላይ የሦስት እርከን ጭማሪ ተጨምሮ ወደ ሚቀጥለው የደመወዝ እርከን ይሸጋገራል፤
2. በቢሮው በየደራጃው በመዋቅር በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ በተደለደሉ ሠራተኞች የሥራ አፈጻጸማቸው አጥጋቢና ከዚያ በላይ ለሆኑት የሶስት እርከን ጭማሪውን የሚያገኙ ይሆናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የደመወዝ እርከን ጭማሪው ሠራተኛው በያዘው የሥራ መደብ ደረጃ ላይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በፊት በተለያየ ምክንያት ገባ ብሎ ሲከፈላቸው ለነበሩ ሠራተኞች ከሦስት እርከን በታች ሲያገኙ ከቆዩ በያዙት ደረጃ ሦስት እርከን ገባ ብሎ እንዲከፈላቸው ይደረጋል፤
4. ቢሮው ፈቅዶላቸው ከአንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ የሚፈጅ ትምህርት ወይም ስልጠና ለመከታተል የገቡ እና እስከ ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በሥራ ላይ የነበሩ ሠራተኞች የዚህ የእርከን ጭማሪ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤
5. ይህ የእርከን ጭማሪ ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ ከሥራ የለቀቁ ሠራተኞች የእርከን ጭማሪው እስከለቀቁበት ጊዜ ድረስ ያለው ክፍያ ሊከፈላቸው ይችላል፡፡

### 7. የእርከን ጭማሪው የማይመለከታቸው ሠራተኞች

1. ከተቀጠሩ ሁለት ዓመት ያልሞላቸው ሠራተኞች ፤
2. ጊዚያዊ ወይም ኮንትራት ሰራተኞችን ፤
3. ቢሮው ፈቅዶለት ለአንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሚፈጅ ትምህርት ወይም ስልጠና ላይ የሚገኝ ሰራተኛ፤

4. ከፍ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ በተጠባባቂነት የተመደበ ሠራተኛ የእርከን ጭማሪ የሚታሰብለት ተጠባባቂ ከመሆኑ በፊት ባለው የሥራ ደረጃ ላይ በመመስረት ይሆናል፤
5. በደረጃ እድገት ተወዳድረው የእርከን ጭማሪው ተግባራዊ እስከ ሆነበት ጊዜ የደረጃ እድገት አግኝተው 9 ወር ያልሞላቸው ሠራተኞች በአንድ ጊዜ ሁለት እድገት መስጠት የማይቻል ስለሆነ የእርከን ጭማሪውን አያገኙም፤
6. በደረጃ እድገት ውድድር ላይ የሚገኙ የተቋሙ ሠራተኞች ደረጃ እድገቱን ካሸነፉ የተወዳደሩበት ደረጃ ላይ ከእርከን ጭማሪ ውጪ እንዲመደቡ ይደረጋል፤
7. በከፍተኛ የዲስፐሊን ጉድለት ከደረጃው ዝቅ ያለ እና ደመወዙ የተቀነሰበት ሠራተኛ የእርከን ጭማሪው የሚሰጠው በተቀነሰው ደረጃ እና ደመወዝ መሠረት ይሆናል፤
8. ከደመወዝ እና ከስራ የታገደ ሠራተኛ ጉዳዩ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የእርከን ጭማሪው አይመለከተውም፤ ነገር ግን ውሳኔው ሠራተኛውን የማያስጠይቅ ሆኖ ከተገኘ በቀድሞ የሥራ መደብና ደረጃ ላይ የሚመለስ ከሆነ የእርከን ጭማሪዉን እንዲያገኝ ይደረጋል፤
9. በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከነበረበት የስራ ደረጃ ዝቅ ተደርጎ የተመደበ ሠራተኛ በተመደበበት የሥራ ደረጃ ካለው ደመወዝ ትይዩ የሚገኘውን የሶስት የእርከን ጭማሪ ያገኛል፡፡ ሆኖም እየተከፈለው ያለው ደመወዝ ከተመደበበት ሥራ ደረጃ የሦስት እርከን ጭማሪው ከሚያገኘው ደመወዝ ጋር እኩል ከሆነ ወይም በላይ ከሆነ ሠራተኛው የያዘውን ደመወዝ እንደያዘ ይቀጥላል፤
10. የእርከን ጭማሪው ተግባራዊ ከተደረገበት ጊዜ በኋላ የሚቀጠሩ ሠራተኞች ቀድሞ ለስራ መደቡ ደረጃ የጸደቀውን ደመወዝ የሚያገኙ ይሆናል፤
11. ይህ የእርከን ማሻሻያ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የሥራ መልቀቂያ ጠይቀው የተሰናበቱ ሠራተኞች የዓመት ዕረፍት በገንዘብ እንዲለወጥላቸው ሲጠይቁ በቀድሞ ደመወዛቸው እየተሰላ የዓመት እረፍታቸው በገንዘብ ሊለወጥላቸው ይችላል፤

## 8. የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ አፈጻጸም

1. የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ ጊዜያዊ ወይም ኮንትራት ሰራተኞችን አይመለከትም፤
2. በቢሮው በየደራጃው በመዋቅር በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ በተደለደሉ ሠራተኞች በስራ መደብ እና ደረጃ ላይ ተመስርቶ የከተማ አስተዳደሩ ውሳኔ ተግባራዊ ከተደረገ ጀምሮ  የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያው ተጠቃሚ ይሆናሉ፤
3. በከፍተኛ ዲስፐሊን ጉድለት ከደረጃው ዝቅ ያለ እና ደመወዙ የተቀነሰበት ሠራተኛ የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ የሚያገኘው በተቀነሰው ደረጃ መሠረት ይሆናል፤

4. ከደመወዝ እና ከሥራ የታገደ ሠራተኛ ጉዳዩ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ማሻሻያው አይመለከተውም፡፡ ነገር ግን ውሳኔው ሠራተኛውን የማያስጠይቅ ሆኖ በቀድሞ የስራ መደብና ደረጃ ላይ የሚመለስ ከሆነ ለደረጃው እና የሥራ መደቡ የተፈቀደውን ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ እንዲያገኝ ይደረጋል፤
5. ተቋሙ ፈቅዶለት ለአንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ የሚፈጅ ትምህርት ወይም ስልጠና ላይ የሚገኝ ሰራተኛ የመኖሪያ ቤት አበል ማሻሻያውን እንዲያገኝ የሚደረግ ሆኖ ነገር ግን ከመኖሪያ ውጭ ያሉ የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያውን አያገኝም፤
6. በተጠባባቂነት የተመደበው የሥራ መሪ ወይም ሠራተኛ ከተመደበበት ጊዜ ጀምሮ በተጠባባቂነት በተመደበበት ደረጃ የተመለከተው ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች አበል ማሻሻያ ይከፈለዋል፤
7. ከፍ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ በውክልና የተመደበ ሠራተኛ የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያ ተጠቃሚ የሚሆነው በውክልና ከመመደቡ በፊት ባለው የሥራ ደረጃ ላይ በመመስረት ይሆናል፤
8. በአመት ፈቃድ እና በራስ ምክንያቶች ከ30 ቀናት በላይ ለሆኑ ቀናት ከስራ ለተለየ ሰራተኛ የመዘዋወሪያ አበል አይከፈለውም፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 9. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. የእርከን ጭማሪው እና የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም አበል ማሻሻያው ተግባራዊ የሚደረገው በቢሮው ዋና መስሪያ ቤት ደረጃ አስራ ሦስት፤ በሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ፤ ደረጃ አስራ ሁለት እና ከዚያ በታች በሰው ሃብት ሥራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ሲሆን በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ደግሞ ለሁሉም ደረጃዎች በሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ በሚፈረም ደብዳቤ ይሆናል፤፤
2. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈነ አግባብነት ያለው ጉዳይ ሲያጋጥም ጥያቄው በሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ በኩል ቀርቦ በቢሮው የበላይ ኃላፊ ወሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፤
3. ማንኛውም ሠራተኛ ለስራ መደቡ እና ደረጃው የተፈቀደውን የጥቅማጥም ማሻሻያ አበል ብቻ ያገኛል፤

### 10. ተጠያቂነት

ይህን መመሪያ የተላለፈ ወይም የጣሰ ማንኛውም አመራር ወይም ፈጻሚ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 11. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ በቢሮው ሊሻሻል ይችላል።

## 12. የመመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቀማጥቅም አበል እና የእርከን ጭማሪ ውሳኔ ለቢሮው ሰራተኞች ተፈጻሚ እንዲሆን ከወሰነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 02 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አደም ኑሪ ዋበላ**